የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን
የሰሜን ምሥራቅ የደቡብ ምሥራቅ እና
የመካከለኛው አሜሪካ የኒውዮርክ ሃገረ ስብከት
ጽሕፈት ቤት

The Ethiopian Orthodox Tewahedo Church
Archdiocese of New York, Northeast, Southeast and
Central United States of America

ቁጥር 135 / Jan 6 2016

ቀን Jan 6 2016

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን

«አ! ትሕትና ዘመጠነዝ ትሕትና?» ወይ ትሕትና ዋ! ትሕትና እንደምን ያለ ትሕትና ነው? «አ! አፍቅሮተ ሰብዕ ዘመጠነዝ አፍቅሮተ ሰብዕ» ወይ ሰው መውደድ ዋ! ሰው መውደድ እንደምን ያለ ሰው መውደድ ነው?

እንዲህ ባለው ሰው መውደድ እና እንዲህ ባለው ፍቅር  የዓለም መድኃኒት ኢየሱስ ክርስቶስ በታላቅ እና በተለየች ትሕትና ፍጹም አምላክ ሲሆን ፍጹም ሰው ሆኖ ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወለደ፤ በጨርቅ ተጠቀለለ፤ ብርዱንና ቁሩንም ታግሦ በበረት ተኛ። ለልማዱ ሕፃናት ሲወለዱ አናት እንዳይወርዳቸው፣ አካል እንዳይዛባባቸውና ዘውረ ዓይን እንዳይገጥማቸው በጥንቃቄ ታቅፈው ይይዟቸዋል እንጂ ወዲያውኑ አያስተኟቸውም። መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ወዲያውኑ እንደተወለደ በግርግም ተኛ። መንክር ወመድምም ወእፁብ ግብር (ግሩም መድምም ዕፁብ ድንቅ ሥራ ነው)።

ዜና ድርሳነ ኤልያስ እንደሚያስረዳው ቴስቢያዊው ነብዩ ኤልያስ ሲወለድ በእሳት ስፋድል ተጠቅልሎ ነው። በዚህም የተነሳ እናት አባቱ ፈርተዋል፤ ደንግጠዋል። ጌታችን መድኃኒታችን ሲወለድ ግን የኤልያስ ወላጆች እንደደነገጡት ቡርክት ማርያም አልደነገጠችም፤ አረጋዊው ዮሴፍም አልፈራም ረዳቷ ሰሎሜም አልተሸበረችም። ከአዳም ሰባተኛ ትውልድ የሆነው ሄኖክ «ወአስከብዎ ለውእቱ ሰይፍ» ያንን ስለት ያንን ኃያል ሰይፍ በበረት አስተኙት በማለት ጌታ በጎል መወለዱን እንዳመለከተው ኢትዮጵያዊው ሊቅ ቅዱስ ያሬድም «እናቱ ቡርክት ማርያም በበለስ ቅጠል ጠቀለለችው አለበሰችው» ይለናል። ይኸውም በእፀ በለስ ምክንያት የወደቁትን አዳምን እና ሔዋንን ካሣ የከፈለላቸው መሆኑን ያጠይቃል።

አቤቱ ኃሻዬ ሆይ ጠላቶቼን በኃይልህ በትናቸው (መዝ. ፶፱፥፲፩) በማለት ነቢየ እግዚእ ዳዊት "ኃሻዬ" ብሎ የጠራው የዳዊት  ኃሻ በቤተልሔም ዋሻ መወለዱ ምን ይገርም! ምን ይደንቅ! አሪት የተገኘችባት ደብረ ሲና ተራራ በጉምና በጢስ፣ በእሳት፣ በነፋስ፣ በጭጋግ እና በድምጸ ነጋሪት ተከብባ ተጨንቃ በመራድና በመንቀጥቀጥ በፍርሃትና በመደንገጥ ነበረች። ኢየሱስ ክርስቶስ የተወለደባት ቤተልሔም ግን  የሰላም፣ የፍቅር፣ የበጎ ነገር ምሳሌ፣ የሕግ መፍለቂያ ቦታ ናት። የሰላም ወንጌልም በእርሷ ተገኝቷል። መምህረ አሪት ሙሴም ስላየው ነገር "ርዑድ ወድንጉፅ አነ - እኔ የምፈራ የምደነግጥ የምርድ የምንቀጠቀጥ ሰው ነበርኩኝ" በማለት ሲናገር የቤተልሔሙ ሰው አረጋዊው ዮሴፍ ግን ሰላም፣ አድናቆትና መረጋጋት ሰፍነውበት ይታይ ነበር።

ክርስቶስ ማለት ንጉሥ ማለት ሲሆን ኢየሱስ ማለት ደግሞ አዳኝ መድኃኒት፣ ንጉሠ ነገሥት፣ እግዚአ አጋእዝት፣ አምላከ አማልክት ማለት እንደሆነ ግልጽ ነው። በቅዱስ ዮሐንስ ወንጌል «ኢየሱስ ናዝራዊ ንጉሠ አይሁድ» ተብሎ ንግሥናው የተገለጸለት ቢሆንም እንደ ንጉሥነቱና እንደ ከህሊነቱ ያማረ ስፍራን አልመረጠም። በጌጥና በክብር ለውበትና ለግርማ መንግሥት ሲባል የጥርሳቸውን ጌጥ ሲፈልጉ ብዙ እልፍ አዕላፋት ዝሆኖች አልቀውለት በዝሆን ጥርስ በተሠራው በሰማርያ በሚገኘው በነ አክአብ ቤተ መንግሥት ልወለድ አላለም (፩ኛ ነገ. ፳፪፥፴፱)። ቡርክት ማርያምም ንጉሠ ነገሥት ንጉሠ ሰላም ኢየሱስ ክርስቶስን በሦስት ሺህ መክሊት ወርቅ በተገዛች በንጉሥ አርጤክስስ የዕንቁ ጽዋ ላጠጣው ሳትል «እንደ ድሆች ልጆች አደገ» ተብሎ እንደተጻፈ እጽፍ ጉንጽፍ ብሎ በተወለደበት በረትም በትሕትና፣ በሰላም እና በፍቅር ተኛ፤ የሰማይ መላእክትና እረኞችም ዘመሩለት። "በበረት የሚተኛ ደሃ ንጉሥ" ብለው ሳይንቁትና ሳያቃልሉት ሰብዓ ሰገል ወርቅ እጣን ከርቤ ገበሩለት። ሰብዓ ሰገል ያመልኩት የነበረው ኮከብም የማያድን መሆኑን አስገንዝቧቸው ወደ እውነተኛው አምላክ አድርሷቸው ተሰውሯል። አ! እመቂሁ ለብዕለ ዝበቢሁ ምልአቱ ስፋቱ ልሕቀቱ ምጥቀቱ እንዴት ይረቃል እንዴትስ ይደንቃል?

መልአከ ሰላም የእግዚአብሔር መልአክ ደቀ መዛሙርቱን እረኞቹን የሰላሙን ድኅ የምስራቹን ድኅ የይትባህሉን መነሻውን እና  መድረሻውን ሲያስተምራቸው **"ምልክቱ ይኸ ነው ሕፃን አውራ ጣቱ ታስሮ በግርግም ተኝቶ በጨርቅም ተጠቅልሎ ታገኛላችሁ"** ብሏቸዋል። አውራ ጣቱን ታስሮ የሚለው ሐረግ በሌሎቹ አብያተ ክርስቲያናት ተጽፎ ባይገኝም በእኛ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ግን በግዕዙም ሆነ በአማርኛው ላይ ተጽፎ ይገኛል።

ZAKARIAS

ብፁዕ : አባ: ዘካርያስ : በኢትዮጵያ · ኦርቶዶክስ ተዋህዶ
ቤተክርስቲያን : በሰ-ሜን ምሥራቅ : ምዕራብ አሜሪካ
የንዮርክ : ሀገረ : ስብከት : ሊቀ : ጳጳስ :

Abba Zekarias, Archbishop of Ethiopian
Orthodox Tewahedo Church Diocese of
New York in Northeast and West U.S.

140-142 W 176th Street Bronx, New York 10453
Tel. 718-466-0600/718-299-2741 Fax 718-466-1271

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን
የሰሜን ምሥራቅ የደቡብ ምሥራቅ እና
የመካከለኛው አሜሪካ የኒውዮርክ ሃገረ ስብከት
ጽሕፈት ቤት

The Ethiopian Orthodox Tewahedo Church
Archdiocese of New York, Northeast, Southeast and
Central United States of America

"አውራ ጣቱን አሰረችው" የሚለው ቡርክት ማርያም ከአንበሶች ዋሻ ከነብሮች ተራራ የወጣች ማለትም ከነቢያት ወገን የተገኘች ነቢይት (ወለተ ነቢያት) ናትና የትንቢት መንፈስ ተገልጾላት በዕለተ ዓርብ ዮሴፍና ኒቆዲሞስ እንዲህ እጅህንና እግርህን ያስሩሃል ማለቷ ሲሆን በጨርቅ መጠቅለሉም ዮሴፍና ኒቆዲሞስ በጨርቅ ይገንዙሃል ማለቷ ነው። ሰሚና አንባቢ ተርጓሚ ሁሉ ይህን ቃል ሊያመሰጥሩት ሊያራቅቁት ሊተረጉሙት ይገባቸዋል። ከላይ ምልክቱ ይህ ነው ብሎ በቅንነት ለደቀ መዛሙርቱ ኖሎት (እረኞች) የነገራቸው መምህረ ሰላም መልአክን እናደንቀዋለን ።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የዜማ፣ የድጓና የቅዳሴ መምህራን ደቀ መዛሙርቶቻቸው የኔታ (የኔ ጌታ) ምልክቱን ይንገሩን ሲሏቸው "እዚያው ተምረህ ድረስበት" ይሉታል እንጂ በምንም ዓይነት አይነግራቸውም ። የሰላም የምሥራች አዋጅ ነጋሪ መልአክ (ቅዱስ ገብርኤል) ግን ምልክቱ ይህ ነው ብሎ ነገራቸው። በዚህም ምልክት ዋና ዋና ሥረዩ እነ ዮም ተወልደ፣ እነ ቤዛ ኲሉ፣ እነ እግዚእ ወመድኅን የመሳሰሉት ሁሉ ይገኙበታል። የእግዚአብሔር መላእክትም ጠባቂዎች አስተማሪዎች መልዕክተኞች መሆናቸው የታወቀ ነው። ጌታ በተወለደ በስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ቅዱስ ያሬድን በሰረገላ ብርሃን ነጥቀው ወደ ዓለመ መላእክት ወስደው ከሥላሴ አቅርበው ድጓ ዝማሬ ተገልጾለት ወደዚህ ምድር መመለሱ ይታወቃል።

ስለ ክርስቶስ ወደ ዓለም መምጣትና ስለ ሰው ልጆች ከመከራ ነፍስ ለመዳን ቀዳሜ ፍጥረት አዳም፣ ርእሰ ባሕታውያን መልከ ጼዴቅ፣ ሊቃነ ነቢያት ሙሴና ኤልያስ እንዲሁም ሌሎች አበይትና ንዑሳን ነቢያት በጸሎታቸው በመሥዋዕታቸው በትንቢታቸው በተስፋቸው ወደ እግዚአብሔር ጮኹ። እግዚአብሔር ጩኸታቸውን ሰምቶ የማዳን ሥራውን እንደሚያከናውን ለኢሣይያስ ገለጸለት። የማዳኑ ምልክት ምን እንደሆነና የክርስቶስ ከድንግል መወለድ በእንዴት ያለ ሁኔታ መሆኑን ሲያመለክታቸው መዳንን ትድናላችሁ ለመዳናችሁም እርሱ ራሱ ጌታ ምልክት ይሰጣችኋል። እነሆ ድንግል ትፀንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች ስሙንም አማኑኤል ብላ ትጠራዋለች (ኢሳ. ፯፡፲፬) በማለት አናገረው።

ነቢየ አእምሮ ኢሣይያስ ጌታችን ክርስቶስ ከድንግል መወለዱንና የመዳንም ምልክት በእርሱ እንደሚሆን በሚገባ ተናግሮ ወደ ሌሎች ትንቢቶቹና ወደ ሌሎቹ አመስጥሮዎቹ አለፈ። ይህ ነቢይ ከዚህ በመቀጠል ብዙ ትንቢትና ምሳሌያትን ምስጢራትንም እየተናገረ ሄዶ ከምእራፍ ፶፫ ቁጥር ፰ ሲደርስ የተናገራቸው ትንቢታትን ወደኋላ ዘወር ብሎ አሰበና "እነሆ ድንግል ትጸንሳለች ወንድ ልጅንም ትወልዳለች ስሙንም አማኑኤል ብላ ትጠራዋለች ብዬ ነበረ የልደቱ ነገር እንዴት በእንዴት ያለ ሁኔታ ይሆን?" እያለ ሲያወጣ ሲያወርድ ተሰጥወ መንፈስ ቅዱስ እንዲህ ሲል መለሰለት «ወመኑ የአምር ልደቶ» ማለትም ቅድመ ዓለም ከአብ ያለ እናት፣ ድኅረ ዓለም ከቅድስት ድንግል ማርያም ያለ አባት የሚወለድ መሆኑን ማን ያውቃል ብሎ መልሶለታል። ነቢየ እግዚአብሔር አቅሙን ያወቀና መጠኑን የመረመረ የማያውቀውንም ለመናገር የማይሞክር በመሆኑ እናመሰግነዋለን።

የተከበራችሁ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ምእመናን የቅዱስ ሉቃስ ወንጌል እንደሚገልጸው በዚያም ወራት ዓለሙ ሁሉ እንዲጻፍ ትዕዛዝ ወጣች ተብሎ እንደተጻፈ የንጉሡን ትዕዛዝ አክብሮ ዓለሙ ሁሉ ስሙን ለማስመዝገብ እንደጎረፈ እኛም ስማችንን በሕይወት መጽሐፍ ለማስጻፍ እና በልበ ሥላሴ ለማሳወቅ ወደ መልካሚቱ መንገድ ወደ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በመገሥገሥ ይህንን የተከበረ ርዕሰ በዓላት የሆነውን ልደቱን ስናከብር ምን ያህል እግዚአብሔርን እየፈራን እና ስሙን እያከበርን ሊሆን እንደሚገባ ለመገንዘብ እያዳግታችሁም ። ይህን በዓል ስናከብር የተራቡትን እና የተጠሙትን ወገኖቻችንን እያሰብን እንድናከብር እያሳሰብኩ የአባትነት መልእክቴን አስተላልፋለሁ።

እግዚአብሔር ከሁላችን ጋር ይሁን፤ የቅድስት ድንግል ማርያም ረድኤት አይለያችሁ!

ብፁዕ : አባ: ዘካርያስ : በኢትዮጵያ : ኦርቶዶክስ ተዋህዶ
ቤተክርስቲያን : በሰሜን : ምሥራቅ : ... አሜሪካ
የኒዮርክ : ሀገረ : ስብከት : ሊቀ : ጳጳስ :

Abba Zekarias Archbishop of Ethiopian
Orthodox ... ch Diocese of
New York in Northeast and West U.S.

140-142 W 176th Street Bronx, New York 10453
Tel. 718-466-0600/718-299-2741 Fax 718-466-1271